# ወደህ ከተደፋህ ፤ ቢረግጡህ አይከፋህ

## ከመዝገብ ማህደር!!

**አቤት እግዜአ!**

**አይን ማውጣት**

**መራኮት ለቅጥፈት**

**የእናት ጡት ለመንከስ መሻኮት**

**ሌባ ለአመሉ ዳቦ መላስ**

**እንደለመደበት መልከስከስ**

**ደፋ ቀና ትርምስ**

**የደም ሐውልት ለማፍረስ**

**አሁንስ ቅጥ አጡ**

**በጣም አይን አወጡ**

**ለዋርዲያነት ይሁን ለግብዣ**

**ምሽታችንን መበረዣ**

**አይጠሩ ስምን ይዘው መጡ**

**እጅግ በጣም ተንበላጠጡ**

**አበላሹት ምሽታችንን**

**ሰማዕታት መዘከሪያችን**

**ደማቸውን ረግጠው ሄደው**

**የተሰውትን ስም አበላሽተው**

ስራቸው የቁም ተዝካር

ከአረጋዊ ጋር ለመዳር

ተኮፈሱብን ከዳር

ማፍረሱን የተካኑበት

ማበላሸቱን ሲያውቁበት

መረዙብን ሚሽታችንን

በአመት አንዴ መገናችን

ሰማዕታት መዘከሪአችን

የገደላቸውን ይዘው መጡ

አሁንስ በጣም ዓይን አወጡ

ብተና የለመዱ

ለጠላት ያጎበደዱ

ወኔ ቢስ ተልካሻ

ደፋ ቀና ሲሉ ለጉርሻ

በረዙብን በዓላችንን

ሰማዕታት መዝከራችን

አይን ቀርጥፎ የበላ

ብልጥ አይሉት ተላላ

አሁን ምን ይባላል

ማወቅ አይሉት አለማወቅ

በምርኩዝ እድሜ መንዘላዘል

የሰማእታቱን ደም ረግጣችሁ

ቀዩን መስመር ጥሳችሁ

በዚያ ያዘነው ሳይረሳ

ጨመራችሁልን ጠባሳ

ትዝታችን እንዳናወሳ

ሴራ በትግሉ ሳይበቃችሁ

መሃላችን ተኮፍሳችሁ

አሁንስ በጣም ቅጥ አጣችሁ

እርግማናችን ይድረሳችሁ

የተቆረጠው አንጀታችን ይፋረዳችሁ

አይን ይብላችሁ

በቁም ያድርቃችሁ

ዘልዛላው እድሜአችሁ አሁንም ያዋርዳችሁ

የቤተክርስቲያን ውሻ ሁኑ

ለዘላለም እዘኑ

የሰማእታት አጽም ይፋረዳችሁ

ቃል ኪዳኑን ከዳችሁ

ከገዳዩ ጋር ዋላችሁ

አጽሙን አስረገጣችሁ

ልታነካኩን ከጀላችሁ

እዚያው በጠበላችሁ እናንተው ተልከሰከሱ

ከወያኔያችሁ ጋር ደግሱ

የገዳያችንን ጫማ ላሱ

የትውልድ አተላ

የጋኔን ምግብ አምቡላ

አሁንስ ከረፋችሁ

በቁማችሁ ሞታችሁ

እድሜ ብዙ ማስተማር ሲችል

የናንተ ግን ተበክሎ ሊበክል

ሲያቅበዘብዛችሁ አየነው

ኤረ ያሁኑስ ምን ጉድ ነው

የትውልድ ማፈሪያዎች

ሙልጭ ያላችሁ ከሃዲዎች

ሂዱ ተጠረጉ

እኛን ግን አታነካኩ

ለገዳያችን ተንበርከኩ

እርማችሁ ይሁን አትድረሱብን

ሳትጋበዙ አትምጡብን

ጽናታችንን አታርክሱብን

እርም አንበላም አለመደብን

እኛስ ምለናል

እርም ላንበላ ቆርጠናል

በቃ ብለናል

የተፋነውን ላንልስ

በሰማዕታት አጽም  ላይ ላናስደንስ

አትድረሱብን አንፈልግም

አንነካካም በናነተ እድፍም

የሰማዕታት አጽም ይፋረዳችሁ

መወሳቸውን አበላሻችሁ

በቁም የሞታችሁ ወኔ ቢሶች

የትውልድ ማፈሪያዎች

አትድረሱብን ሁለተኛ

እናንት ተግባረ መናኛ

ታሪክ ይፋረዳችሁ

የቁም ሞት ይግደላችሁ

ንስሀውንም ይንፈጋችሁ

የቤተክርስቲያን ውሻ ከሆናችሁ

ወዳችሁ ከተደፋችሁ

ብንረግጣችሁ አይክፋችሁ